# ለሶስት ልጆቻቸውን ሦሥት ሞግዚቶች ስላላቸው ኢትዮጵያውያን ወላጆችና ስለሶስቱ ልጆቻቸውን ቅንጦት

ግርማ ወልደማርያም

**( 15 March 2016)**

በሞያቸው ምክንያት ከአውስትራሊያ ወደ ድቧይ ሄደው እየሰሩ የሚኖሩ - ለአገራቸውና ለሕዝባቸው በጣም ተቆርቋሪ ባልና ሚስት ወዳጆቼ 'ስለዚህ አርእስት' በወሬ ሽቦ (በሥልክ) ያጫወቱኝን ስለገረመኝ ፤ እኔም በተራዬ ለጥቂቶች በወሬ ሽቦ ከመንገር በጽሐፍ አደባባይ እንድወጣው አእምሮዬ አስገደደኝ ።

እነኚህ ዱባይ የሚኖሩትን ባለትዳር ወዳጆቼ እንደምንም ተፍጨርጭረው በዓመት አንድ ቀን በከተማቸው ሁነኛ የልጆች መዝናኛዎች ወደ አሉበት ወስደው ልጆቻቸውን ያዝናናሉ ። ስለሆነም በዚህ በያዝነው ዓመት የእኛ ገና በዓል አካባቢ ሶስት ልጆቻቸውን ይዘው ለእያንዳንዳቸው በሰዓት $100 ዶላር ከፍለው ልጆቻችውን እያዝናኑ እያሉ ፤ ከሌሎች እዚያው ሶስት ልጆቻቸውን ከሚያዝናኑ ኢትዮጵያውያን ባልና ሚስት ጋር በሩቅ ይተያያሉ ።

ከዚያም በኢትዮጵያዊ/ዊትነት ቀለማቸውን ተሳስበው ፣ አራቱም ወደፊት ተራምደው አንድ አንጻራዊ መካከል ላይ ተገናኝተው በአማርኛ ቋንቋ ሰላም! ሰላም ! ተባብለው ተጨባበጡ ። ወንዶቹ ተዋውቀው ጫወታ ለመጀመር ዳርዳር በማለት ላይ እያሉ ፤ እንስቶች ቶሎ መግባባት ስለሚችሉ ሁለቱም እንስቶች ወዲያዉኑ ተግባብተው መጫወት ጀመሩ ።

ቀጥሎም ከመጀመርያ ደረጃ መግባቢያ ጫወታ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ማለት የት እንደሚኖሩና ኑሯቸው ማለት የመደብ ጀርባቸው ምን እንደሚመስ

መጫወት ሲጀምሩ ፤ ወይዘሮ አሰገደች(እኔ የፈጠርኩት የውሸት ስም) ከእነቤተሰብዋ ዱባይ የምትኖር መሆንዋና በምን ሞያ ዘርፍ እንደ ምትሰራ ገልጻ ስትጨርስ ፤ ያችኛዋ በተራዋ የት እንደ ሚኖሩና ስለቤተሰብዋ ኑሮ ምን እንደሚመስ እንደሚከተለው ገለጸችላት።ይኸውም ፡-

- ኢትዮጵያ እንደሚኖሩ

- የዱባይ ሕጋዊ የመኖርያ ፍቃድ እንዳላቸው (ፐርማነንት ረዝደንሲ) እንዳላቸው

- ለሶስቱ ልጆቻቸው ሦሥት ሞግዚት እንዳላቸው

- የሚቆዩት በዱባይ ከተማ ከሚገኙት ምርጥ የቅንጦት (luxury) ሆቴሎች አንዱ እንደሆነ

- ለገና እረፍት ት/ቤቶች ተዘግተው - ልጆቻቸውን እዚያ ከመውሰዳቸው በፊት እሷና ባልዋ ለሶስት ሳምንታት ተዝናንተው ወደ ኢትዮጵያ እንደተመለሱ

- ከልጆቻቸው እረፍት በፊት ሁሌ እነሱ ተዝናንተው ወደ ቤታቸው እንደሚመለሱ

- ለገናና ለፋሲካ እረፍት ት/ቤቶች ሲዘጉ ፤ ምርጥ የልጆች መዝናኛ ወዳሏቸው የተለያዩ አገሮች እንደሚወስዷቸው

- በየዓመቱ ረዥም (3 የክረምት ወራት) ት/ቤቶች ሲዘጉ ልጆቻቸውን ይዘው ወደ አሜሪካ እንደሚሄዱና ከእነልጆቻቸው ባለአምስት ኮከብ ወይም አቻ ሆቴል እንደሚቆዩ

- በየዓመቱ ለሶስት ሦሦት ወራት አሜሪካ በሚቆዩበት ወቅት ልጆቻቸው ልዩ (በጣም ወድ) ት/ቤት ልከው ወይም ምርጥ አስተማሪዎች ቀጥረው እንደሚያስተምሯቸው

- በአሜሪከ በጣም ወድ መዝናኛዎችን ያሉበት ቦታ ወስደው እንደሚያዝናኑውቸው

- ስለገንሀብ አንስተው ሲያወሩ ፤ገንዘብ ያለው ኢትዮጵያ ነው እንዳሏቸው

- የእነዚህ ባልና ሚስት ሥራ ምን እንደሆነ ነግሯችኋልን? በማለት ስጠይቃቸው፤ ጥሩ ሥራ እንዳላቸው ነገሩን እንጂ የሥራቸው ዓይነት ሊነግሩን አልፈለጉም አሉኝ

-ስማቸው አልነገሯሁምን? ነግረውናል ነገር ግን እውነተኛ ስማቸው ላሆን ይችላል ብለን ጠተራጠርን፤ የሰጡን ስም እውነትም ይሁን እውሸት ባልነግርህ እንመርጣልን፤ምክንያቱም በዓመት አንዴ ቤተሰብ ለመጠየቅ አገር ቤት ስለምንሄድ ።

- የእነዚያ ባልና ሚስት ዕድሜ መገመት ትችላላችሁን? ከ 38-45 የዕድሜ ክልል ወስጥ ያሉ ናቸው አሉኝ

-እናንተ የምትኖሩት በዘይት ሃብት እጅግ በጣም በበለጸገ አገር ነው ፤ የተባበሩት አረብ ግዛቶች መሳፍንቶች ንጉሥ 'ዘይድ ብን ሱልጣን አልናሂያን'- (United Arab Emirates Sultans king Zayed Bin Sultan Alnhyan) ልጆች እያንዳንዳቸው አንድ ሞግዚት ነበራቸውን ? አልሰማንም ግን ለማጣራት እንሞክራለን አሉኝ ።

በዝባዥና ተበዝባዥ፣ ገዢና ተገዢ ማኅበረሰብ ከተከሰተበት የታሪክ ምዕራፍ አንስቶ ፤በየትኛውም አገር ፍጹም ሃብታሞችና አንጻራዊ ሃብታሞች እንዳሉ ሁሉ ፍጹም ድሆችና አንጻራዊ ድሆች ነበሩ፣ አሉ፣ ይኖራሉም ። ይሁን እንጂ ከአሥራምስት እስከ ሃያ ሚሊዮን የሚሆኑትን ኢትዮጵያውያን በቀን አንድ ጊዜ የሚቀምሱትን ጥራጥሬ ባጡበት አገር ፤ በዚህ ዓይነት ፍጹም በናጠጠ ቅንጦት የሚኖሩ ልዩ ዜጎች መኖራቸውን አያስገርምም?

የዚህ ዓይነት የደለበ ሃብት ምንጭ ከየት ይሆን? ከቤተሰብ የተወረሰ? ከንግድ ዘርፍ? ከሆነስ በአሁኑ ኢትዮጵያ በንጹህ ነግዶና አትርፎ ማለት ሙስና ሳይታከለበት ቤተሰብ በዚህ መልክ የሚያዝናና ሃብት ማግኘት ይቻላልን? ያለቀረጥ ወይም ግብር በሚፍልጉት የንግድ ዘርፍ አስመጭና ላኪ እና ያለወለድ የሚፈሉጉትን ያህል ገንዘብ ከባንክ ወስደው ከሚነግዱትን የወያኔ ቤተሰብ አንዱ ከእነቤተስቡ ይሆን? ከገዢዮቻችን ጋር በአምቻና በጋብቻ የተገናኙ ይሆኑ ይሆን? ከቁንጮ ገዥዮቻችን አንዱ ከእነቤተስቡ ይሆን? በአሁኑ ሃገራችን የእነዚህን ዓይነት የቅንጦት ሕይወት የሚኖሩ ስንት ይሆኑ ? 1/3 ኛውን ወይም 1/4 ኛውን የማኅበረሰቡ አባላት በረሃብ ከሚሞትበት ሌሎች አገሮች፤ እንደ እነዚ ዓይነት እጅግ በጣም በተሥፈነጠረ ቅንጦት የሚኖሩ የማኅበረሰቡ አካል ይኖሩ ይሆን?

ገንዘብ ያለው ኢትዮጵያ ነው ማለታቸው ምንን ይጠቁማል? የገንዘብ ችግር ያለበቸው ኢትዮጵያውያን የሉም ማለታቸው ይሆን? የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ እንደ ፍላጎቱ በልቶ፣ ጠጥቶ፣ ለብሶና ተዝናንቶ ይኖራል

ማለታቸው ይሆን? የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ እነሱ የሚኖሩትን ዓይነት ኑሮ ይኖራል ማለታቸው ይሆን? ከ 15-20 ምሊዮን ረሃብተኛ ኢትዮጵያውን አሉ መባሉ አልሰማንም ወይም ተረትተረት ነው ማለታቸው ይሆን? የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚራበው በር አጥቶ ሳይሆን ወደ ገበያ ወጥቶ መሸመት ሰንፎ ነው ማለታቸው ይሆን?

ንጽጽሩ ያልተጣጣመ ወይም ያልተቀራረብ ካልሆነብኝ በስተቀር፤ የእነዚህ ቅንጦተኛ ኢትዮጵያውያን ሕይወትና የወቅቱ ኢትዮጵያውያን ረሃብተኞች ኑሮ ከበርካታ ታሪካዊ ይሁንታዎች ጋር እንዳነጻጸር ጋብዞኛል።

- ማክሲም ጎርኪ እና ቶልስቶይ ሊዮ ፤ ማክሲም ጎርኪ (Maxim Gorky) እ.አ.አ በ 1868 ዓ.ም ተወልዶ በ 1936 ዓ.ም የሞተ ሩሲያዊ ደራሲ ነው ። ድህነት ቅስማቸውን ከሰበራቸው ቤተሰብ የተወለደ ስለነበረ፤ ከዘጠኝ ዓመት ዕደሜው ጀምሮ ፤ በጫማ ጠራጊነት፣ በመንገድ ጠራጊነት፣በኩሊነት ፣ በሱቅበደረቴነት፣ በዳቦ ጋጋሪ ቤት፣ምስላ ምስሎች በሚሡሩባቸው ሱቆች፣ ከሞሉ ወንዞች ሰዎችን በማሻገር ወዘተርፈ ሥራዎች ራሱን እያስተዳደረ ወደ በጣም ዝነኛ ደራሲነት የተሸጋገረ ሰው ነው ። የሚውለወም የሚያድረውም የዕለት ጉርሻቸውን ለማግኘት ስብዕናን በሚነኩና ዝቅ በሚያደርጉ ሥራዎች ላይ ከተሰማሩትን ፍጹም ድሆች ጋር ነበር ። በተለይም 'እናት' (mother) በተሰኘው መጻፉ የያኔው ሰፊዩ የሩሲያ ሕዝብና ሠራተኛውን የከፋ ድህነት፣ ጉስቁልና፣ ኢፍትህአዊነት፣ ውርደት፣ የሩሲያ አብየት በአውደ ሕዝቡ ላይ ያስከተለውን ጉዳትና መከራ አብጠርጥሮ ጽፏል ፤ የጻፈውም በስደት አሜሪካ በነበረበት ወቅት ነው። ስለእናት (mother)ሳይሰማ/ሳትሰማ በ (ኢ ሕ አ ፓ) የሕዋስ ውይይት ያለፈ/ያለፈች ያለ አይመስለኝም፤ በተለይም ወጣት የኢሕአፓ አባላት ለነበሩት።

ቶልስቶይ ሊዮ (Tolstoy Leo) ወይም ሊዮ ቶልስቶይ እ.አ.አ ከ 1828 -1910 የኖረ ዝነኛ ሩሲያዊ ደራሲ ነው። ይህ ደራሲ ከሚታወቅባቸው መጻሕፍቶቹ አንዱ 'ጦርነትና ሰላም' (War and Peace) ነው ። ቶልስቶይ ከመሳፍንት ቤተሰብ በመወለዱ ከገዢዎች ቤተሰብ ጋር ያደገ፤ ሩሲያዊ ያልሆኑ ምርጥ

አስተማሪዮች ተቀጥሮለት እቤት እየተማረ በከፍተኛ ቅንጦት ያደገና የኖረ ሰው ነበር። በመሆኑ ማክሲም ጎርኪ ስለሩሲያ ሕዝብ ኑሮ የጻፈውን በመጻረር " ሃሳባዊ፣ ፈጠራዊ፣ ስሜታዊ እይታ፣ እውሸት፣ የጀገነነ አስተሳሰብ፣ ጭብጥ ያልሆነ፣ ማክሲም ጎርኪ ከእነ-አስተሳሰቡ ሩሲያዊ አይደለም፣ሩሲያውያን በዛ ዓይነት ድህነት አልኖሩም" ወዘተ.. በማለት ጽፎበታል።

- ሜሪ አንቶኔት (Marie Antoinette) እና የተራቡ ፈራንሳዊያን፤ለሥርወ መንግሥት ለውጥ አብዮት ስለተካሄደባቸው አገሮች ሲነሳ በአንጋፋነት ወይም በበኩር አብዮተኝነት የሚነሳው እ.አ.አ ከ 1789—1799 የተናወጠው /የታመሰው የፈራንሳውያን አብየት ነው ። በዘመናዊ ትምህርት ያለፍነው አብዛኞቻችን እንደምናውቀው፤ ሥርወ መንግሥቱን የተያዘው በንጉሥ በልዊዝ 16 ኛውና በሚስቱ ንግሥት ሜሪ አንቶኔት ነበር። የሚገዙትን ሕዝብ ያመጸው ስለተራብ መሆኑን ሲነገራት " ዳቦ ከሌለ ለምን ኬክ አይበሉም" አለች ይባላል ። ንግሥትዋ ያ ያለችበት ምክንያት፤ በዚያ ዘመን 'ኬክ' የድሆች ወይም የሰፊው የፈራሳውያን ምግብ ነበር ማለት ይሆን? የኬክ ዋጋ ከዳቦ ዋጋ ይረክስ ስለነበረ ይሆን? ሕዝቡ ዳቦ የሚፈልገው ኬክ መብላቱን ሰልችቶት እንደሆነ ማለትዋ ይሆን? ኬክ ሁልጊዜ አግኝታ የመብላት ዕድል ስለነበራት፤ ኬክ የንጉሳዊያንና የሃብታሞች የቅንጦት ምግብ መሆኑን ስለማታውቅ ይሆን?

- የኃይለሥላሴ የ 80 ኛ ዓመት ልደት በዓላቸው እና የወሎና የትግራይ ክፍለ ሃገሮች ረሃብተኞች ፤ በወሎና በትግሬ ክፍለ ሃግሮቻችን ከ 200 000 በላይ ወገኖቻችን የሚቀመስ እህል የሚጎነጭ ውሃ አጥተው እየሞቱ ባሉበት ወቅት ኃይለሥላሴ የ 80 ኛው ዓመት ልደት በዓላቸውን በሥልጣናቸው ዙርያ ካሉት ጋር በውስኪ፣ በኮኛክ ፣ በሻፓኝ ፣ በጮማ ወዘተርፈ እየፈነጠዙ እንደነበረ እንግሊዝአዊው የ(BBC ጋዜጠኛ ጆናታን ዲምበልባይ) ማጋለጡን የሁላችን የትላንት ትዝታ ነው።

- የመንግሥቱ 10 ኛውን የሥልጣን ዘመን ልደት እና የድርቅ ረሃብተኞች ሞት ፤ እ.አ.አ 1984 ዓ/ም የተከሰተውና የዓለምን ሕዝብ ዓይን የሳበው አስከፊ ድርቅ በግምት የአንድ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ሕይወት የቀጠፈ መሆኑን አንዳንድ የአውፓውያን ጋዜጠኞችና እርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ዘግበውታል። ያንን ድርቅ ያስከተለውን ረሃብና ሞት፤ ፋሽስቱ መንግሥቱ ኃለማርያም

“ትናንሽ የሰዎች ችግሮች” “petty human problems” ብለውታል በማለት የያኔ የድርቅና መልሶ የማቋቋም ሃላፊ የነበሩትን አቶ ዳዊት ወደልደ ጊዮርጊስ በማስታወሻቸው (memoirs) እንደጻፉት ይነገራል ። በመንግሥቱ ደም አንዳችም ስብዕናና ርኅራኄ ስለሌል እንካንስ ለረሃብተኞች ሊያዝን፤ በኢትዮጵያ አንድም የተራበ ሰው የለም በማለት የእርዳታ ሰጪ ድርጅቶችን ቶሎ እንዳይደርሱ አስተጓጎሏል። ከዚያ ይልቅ መንግሥቱ የተወጠረው መፈንቅለ አብዮት አድርጎ ሥልጣን ላይ የተቆናጠጠበትን  የመስከረም ሁለት 10 ኛውን ዓመት ‘ፋንጣዚያ ድግሥ ዝግጅት ላይ እንደነበረ በውቅቱ የባዕዳን አገር ጋዜጠኞች ዘግበውታል ።

ይህ ጽሁፍ ሳይተዋወቁ በምድር ገነትና በምድር ሲዖል ስለሚኖሩትን የአንድ አገር ዜግዎች ምሳሌዎችን ያንጽባርቃል።

በተባበሩት/በፌድሬተድ አረብ ኢመሬት የቋሚነዋሪነት(ፐርማነንት ረዝደንሲ) ማግኘትን በተመለከተ

በተባበሩት/በፌደሬት አረብ ኢመሬት (U.A.E)ቋሚ የመኖርያ ፈቃድ ያላቸው በርካታ ኢትዮጵያዊ/ ዊት ሃብታሞች ፣ ባልስልጣኖችና የባለሥልጣኖች ቤተሰብ ይኖራሉን? አው እንዳሉ ይወራል፤ እኛም እናያቸዋልን፤ ቁጥራቸውም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ነው።  እኛ ባለንበት አገር ብቻ ሳይሆን የሌሎች ሃብታም አረብ አገሮች - የክዌት፣የካታር፣የሳውዲ ወዘተርፈ መኖርያ ያላቸው  የውያኔ ባለሥልጣኖችና ቤተሰባቸው፣የእነሱ ጎሳ ሃብታሞች እና የእነሱ ታዛዥ የሆኑ ሃብታሞች በጣም ብዙ ናቸው አሉኝ ። በእነዚህ ሃብታም የአረብ አገሮች የቋሚ ነዋሪነት ፈቃድ ማግኘት ቀላል ነውን? ለእንደኛ ተራ ሰው ከባድ፤እንደ ወያኔ በሻጣ ዶላር ተሸክሞ ለሚመጣ ግን ቀላል ነው። ኢትዮጵያ እየኖሩ የባዕዳን አገራት የመኖርያ ፈቃድ የሚወስዱበት ምክንያት ለምን ይመስላችኋል? የኢትዮጵያ ሕዝብ የተባበረ ክንድ፣ እምባና አድባር፣የኢትዮጵያ ምድርና ሰማይ አድባራት አብሮና ተባብሮ ወያኔዎች በቃችሁ ሲላቸው ለመሸሸጊያ ነው አሉኝ፡፡

ማሳሰቢያ፤ በዚህ ጽሑፍ የትምህርተ ጥቅስ ሥርዓተ ነጥብ አልተጠቀምኩም፤ምክንያቱም- (1) የዚህ ጽሁፍ ምክንያት ስልሆነኝ አርእስት ሲገልጹልኝ ቃላቸውን እንዳል አልወሰድኩም (2) እውነተኛ ሰማቸውን አልተጠቀምኩም።

ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል እንደሚባለው፤አገር ቤት የአዛዥነትን፣ የደለበ ገንዘብ የሚገኝበትን፣ ብዝበዛ ያለበትን፣ ጥሩ ሞያና እውቀት ያሉበትን ወዘተርፈ ድረጅቶች፣ ቢሮችና ተቋማት የእኔ ጎሳ የሚሏቸውን ሲያስቀምጡ በተጓዳኝ በባዕዳን አገሮች የወያኔ ጎሳ አባላት --በቁጥር፣በእውቀት፣በሁነኛ ሥራ፣የባዕዳን አገራት ባልሥልጣናት በመጠጋት፣ በከፍተኛ ትምህርት፣በንግድ፣ በሃብት ወዘተርፈ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን በልጠው እንዲገኙ እና የቀውጢ ወቅት መደበቄያቸውን በማመቻቸት--የአገራችንን በትረመንግሥት ከጨበጡበት ማግሥት አንስቶ (የወያኔ ቁንጮዎች) ይህ ቀራቸው የማይባል ጥረት አድርገዋል እያደረጉም ነው ።

ወያኔ የእኔ ናቸው የሚላቸውን ወደ በሃብት የበለጸጉ አገራት ከሚልክበት በረካታ ዘዴዎች ጥቂቶቹ ፡-

ሀ. በፖለቲካ ምክንያት መንግሥት ይፈልገዋል/ይፈልጋታል የሚል የማስጠንቀቂያ ጽሑፍ አዘጋጅቶ በመስጠትና ወደ ጎረቤት አገራት በመስደድ ነው። ህወሃት ገዢያችን በሆነ ማግሥት  ከጥቅም ውጭ ናቸው በማለት የቀነሳቸውን በጣም ብዙ የህወሃት  ተዋጊዮች ይፈለጋል/ትፈለጋለች የሚል ጽሑፍ አሳቅፎ  ወደ ሱዳንና ኬኒ ሸኛቸው። ስለሆነም የስደተኞች ድርጅቶችና ረሴትልሜት(resettlement) ሰጪ አገራት እወነት እየመስላቸው ያለምንም ችግር  ይቀበሏቸው ነበር፤ ከእነቤተሰባቸው ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የህወሃት አባላት ወደ አውስትራሊያ መጥቷል እየመጡም ነው ።

ለ. በኢትዮጵያ ከኤርትራውያን ስደተኞች ጋር በመቀላቀልና ለእነሱ የመጣውን ሪሴትልሜንት(resettlement) ዕጣ በመሻማት

ሐ.በመንግሥታዊ ሉዕክነት ወደ ሃብታም አገሮች ተልከው -ጥገኝነት ጠይቀው እዚያው እንዲቀሩ በማድረግ

መ. ሃብታም አገሮች ከሌሎች አገሮች ለኢንቨስትሜንት የሚሄዱትን ነጋዴዎች ያወጡትን የነዋይ መሥፈርቶችን አሟልተው እንዲሄዱ በማገዝ፣ ለምሳሌ በአውስትራሊያ የወያኔ ጎሳ ያልሆኑትን

ኢትዮጵያውያን ነጋዴዎች ክራይ ከፍለው መነገድ በማይችሉባቸው በጣም ወድ መናኸርያዎች ንግድ ሲከፍቱ የሚታዩት የወያኔ ጎሳዎች ናቸው

ሠ.አንድ/ት ኢትጵያዊ/ት አንድን ሃብታም አገር ለመጎብኘት የሚያስችሉ መስፈርቶችን በማመቻቸትና እዚያው እንዲቀሩ በማድረግ፤ ከአገር ቤት በመጡ ዓመት ባልሞላው ጊዜ ንግድ ይከፍታሉ፣ የሚኖሩበትና የሚያከራዩትን ሕንጻዎች ይገዛሉ

ረ.በስራፈትነት ገቢ (unemployment benefit) የሚኖሩትን ጨምሮ አገር ቤት ሕንጻ ቤት /villa house ያልገዛ የወያኔ ጎሳ የለም

http://www.ethiopanorama.com